# የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ
# የብሔራዊ ምክር ቤት አባል የሆኑት
# አቶ አብዩ በለው ተከሰሱ፡፡



የአንድነት ፓርቲ የሥራ እንቅስቃሴና ጥንካሬ ያሰጋው ገዥው ፓርቲ ወያኔ በአባላቱ ላይ የሚያካሂደውን ወከባ እንደገፋበት ነው፡፡ ፓርቲው ፅ/ቤት በከፈተባቸው ክልሎች ባጠቃላይ አባላቱን በማዋከብና በማሰር ላይ ሲገኝ፤ በቅርቡ ደግሞ በማዕከል የብሔራዊ ምክር ቤት አባል የሆኑትን አቶ አብዩ በለውን "ህገ-መነግስቱንና ህጋዊ ሥርዓቱን በሃይል ለመናድ" በሚል የፈጠራ ወንጀል ለሰኞ መጋቢት 21 ቀን ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ መጥሪያ ደርሷቸዋል፡፡

ከአዲስ አበባ ያሉ ምንጮቻችን እንደገለጡልን ከሆነ፤ወያኔ አቶ አብዩን፤ የካቲት 20 2001 ከመኖሪያ ቤታቸው አፍኖ በመውሰድ ለአራት ቀናት ባልታወቀ ሥፍራ በማሰር፤ አንድነት ፓርቲን ለቀው ኢህአዴግን እንዲያገለግሉ ሲያግባባና ሲያስፈራራ ነበር፡፡ አቶ አብዩ በዚህ እንግልት አለመበገራቸውን ሲያውቅ፤ - አሳይሃለሁ - በሚል ዛቻ ለቋቸዋል፡፡ በተለቀቁ በ15ኛው ቀን፤ ለሁለት ዓመታት ያህል ተዘግቶ የነበረ የክስ ፋይል አገላብጦ ድጋሚ በመክፈት፤ለሰኞ መጋቢት 21 ቀን/ ማርች 28 2009/ ሁለተኛው ወንጀል ችሎት ከፍተኛው ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ መጥሪያ ሰቷቸዋል፡፡ አንድ አንድ የህግ ባለሙያዎች እንዳብራሩት ከሆነ፤ ክሱ ከ 10 ዓመት እስከ ዕድሜ ይፍታህ ድረስ ሊያስቀጣ የሚችል ነው፡፡

ክሱ ተመስርቶ የነበረው በጥቅምት 24 1999 የቅንጅት አመራር አባላት በቃሊቲ በነበሩበት ወቅት ነው፡፡ በወቅቱ፤ አቶ አብዩን የደህነነት አባላት ለ10 ቀናት ያህል በጨለማ ቤት እስሯቸው የነበረ ሲሆን፤ አቃቤ ህግ፤ ማስረጃ ሊያቀርብ ባለመቻሉ፤ በአንድ ሺህ ብር ዋስ ተለቀው ነበር፡፡ የክሱ ድጋሚ መነሳት፤ፖለቲካዊ ይዘት ያለው መሆኑን ታዛቢዎች ይተነትናሉ፡፡ በተለይም አቶ አብዩ ታፍነው የተወሰዱት፤ ብሔራዊ ምክር ቤቱ፤ ወሳኝ የሆነ ስብሰባ ሊያካሂድ አንድ ቀን ሲቀረው መሆኑና፤ከወይዘሪት ብርቱካን መታሰር ጋር በተያያዘ፤ ፓርቲው እንቅስቃሴ እያደረገ ባለበት ወቅት መሆኑ፤ጥርጣሬውን የጎላ ያደርገዋል፡፡

አቶ አብዩ በለው፤ የ32 ዓመት ወጣት ሲሆኑ፤ በትምህርታቸው በጂኦ ፊዚክስ የማስተርስ ዲግሪ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በ1998 አግኝተዋል፡፡ በሙያቸውም፤ የማዕድንና ኢነርጂ ከፍተኛ ኤክስፐርት ሆነው በሚኒስትር መስርያቤት ውስጥ እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡ ከዚሁ ሥራቸው ጋር በተያያዘም በአሁኑ ወቅት ስዊዲሽ ጂኦሎጂካል እና የደቡብ ክልል መንግስትን በአመካሪነት እያገለገሉ ነው፡፡

በፖለቲካዊ ተሳትፎዋቸውም፤ በቀድሞው ቅንጅት በአሁኑ ደግሞ አንድነት ፓርቲ ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ አላቸው፡፡ በተለይም በአንድነት ፓርቲ ውስጥ የወጣቱ ተሳትፎ በቁጥርም በጥራትም ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዲደርስ እየጣሩ ያሉ ናቸው፡፡ የሳቸው መከሰስ፤ የወጣቱ ተሳትፎ ላይ ያነጣጠረ ነው የሚሉ ታዛቢዎች አሉ፡፡

የአውደ ኢትዮጵያ አዲስ አበባ ዘጋቢያችን፤ አቶ አብዩን አነጋግሮ እንደተረዳው ፤ ግለሰቡ ወደ ውጭ ሀገር እንዲሰደዱ በመንግስት የደህንነት አባላት በቀጥታና በተዘዋዋሪ ጫና ይደረግባቸው ነበር፡፡ በአቶ አብዩ እምነት፤ የመጥርያ ወረቀቱ የ10 ቀን ጊዜ የተሰጠው፤ በፍርሃት ከሀገር እንዲሰደዱ ለማድረግ ነው፡፡ ሆኖም ግን፤ አቶ አብዩ እንዳሉት፤ ምንም የሰሩት ወንጀል ባለመኖሩና የቅንጅት አመራሮች በተለቀቁበት ወቅት፤ በተመሳሳይ ይዘት የተከሰሱ ሁሉ ፋይላቸው እንደሚዘጋ በመገለጹ፤ መንግስት ምንም የክስ መሰረት ስለሌለው፤ ወደ ፍርድ ቤት መሄዱን መርጠዋል፡፡ በይበልጥም፤ በፓርቲው ውስጥ ባላቸው የጎላ ተሳትፎ፤ ያንን ሥራ ትተው ስደትን እንደማይመርጡ፤ በፓርቲው ውስጥም ላሉ ወጣት ታጋዮች ተስፋና አራአያ መሆን እንደሚፈልጉ፤ ወ/ት ብርቱካንም ብቻዋን እንዳልሆነችና የፈተና ጊዜ አጋር እንዳላት እንድታውቅ እንደሚፈልጉ ገልጸዋል፡፡

አውደ ኢትዮጵያ የአቶ አብዩን የፍ/ቤት ውሎና ተከታታይ ሂደቶችን እንደምትዘግብ ከወዲሁ እያሳወቀች፤ ለአቶ አብዩ በለው፤ ብርታትን ጥንካሬንና ፍትህን ትመኛለች፡፡